ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት. ዴ. ፓ)
Tigray Democratic Party (T.D.P)

የህወሓት አመራርና "የፌደራሊስት" ሃይሎች ጥምረት፣ "ያላቻ-ጋብቻ"

የፌደራሊስት ሃይሎች ነን የሚሉ 35 "ድርጅቶች" በትግራይ ክልል ዋና ከተማ መቐለ ከጥር 4-5 ቀን፣ 2012 ዓ/ም ተሰብስበው ጥር 6 ቀን፣ 2012 ዓ/ም የህብረ-ብሄር ፌደራሊስት ሃይሎች ጥምረት፣ ዓላማ፣ ስትራተጂና የትግል ስልት (ማኒፌስቶ) አፅድቀዋል። 80% የትግራይ ህዝብ "ሴፍቲ-ኔት" በተባለው ድር ተጠርንፎ በእርዳታ (ምፅዋት) እህል አስከፊና አስፋሪ ኑሮ እየገፋ ባለበት ወቅት ከድግሱ ወጪ ጀምሮ እስከ የጥምረቱ ቅንብር የቻለው የህወሓት አመራር ነው። ለመሆኑ የህወሓት አመራር ይህ "የፌደራሊስት" ሃይሎች ጥምረት የሚለው ቅንብር እውነት ፌደራሊስት ከመሆን ተነስቶ የመሰረተው ነውን? ዋናው ዓላማውስ ምንድነው? የሚሉት ጥያቄዎች ስናነሳ ለመልሱ ብዙ ርቀት ሳንሄድ በህወሓት ስራ አስፈፃሚ አባል አቶ አስመላሽ ወ/ስላሴ አገላለፅ "ፌደራሊዝምን የመሰረተው ህወሓት ይመራዋል።" ይላልና።

ገና ከጅምሩ የአቶ አስመላሽ ህወሓት የመሪነቱን ብሎም የበላይነቱን እርካብ ስላወጀ፣ በእኩልነት መመስረትን የሚጠይቀው የፌደራሊዝም መርሕ ድራሹ ጠፍቷል። ጥምረቱ የፌደራሊስት ስም ያጠለቀ እንጂ ይዘት የሌለው "ያላቻ-ጋብቻ" መሆኑ ወደ ዝርዝር ሳንገባ መገንዘብ ይቻላል።

ቀጥሎ የተከሰተው አስገራሚ ጉዳይ አጠቃላይ የጥምረቱ የማንነት ስያሜ ላይ እንደ ጥያቄ ተነስቶ እንደ መከራከሪያ ነጥብ ሆነ። "የኢትዮጵያ ህብረ-ብሄር ፌደራሊስት ሃይሎች" የሚሉ ወገኖች ብቅ ሲሉ እነ አቶ አስመላሽና አጃቢዎቻቸው (የመኢብን- መስፍን፣ የኦብኮ- ቶሎሳ ተስፋዬ፣ የኢዴአን- ጉዑሽ ገ/ስላሴ፣ የቅዱፓ- አጀበው ወርቅነህ፣ የኢድህ- ገብሩ በርሄ፣ የኢኮፓ-ገረሱ ገሳ፣ የኦአግ- ዶ/ር ፉሪስ፣ የኢትፓ-ሰለሞን ታፈሰ፣ የሲአን- ዶ/ር አየለ አሊቶ፣ የአብሸ-አላምረው፣ የክሃህ-የማነ አሰፋ ወዘተ) የኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ መጨመር የለበትም፤ አያስፈልግም እንዲሁ "ህብረ-ብሄር....ጥምረት" ብቻ ይባል ብለው አጥብቀው ተከራከሩ። ኢትዮጵያዊነትን መጠየፍ እርቃኑ የወጣ የሃገር ክህደት ይሉታል ይህ ይመስላል። ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ አንዳንዶቹ ሃገር-ወዳድ ግለሰቦች "የኢትዮጵያ" የሚል ስያሜ ካልተሰጠው ከዚህ ጥምረት እንወጣለን ብለው ስለዛቱ የህወሓት አመራር እኩይ ዓላማው እንዳይጨናገፍ ከሚል እሳቤ "የኢትዮጵያ" የሚለው ስያሜ ሳይወዱ ተቀብለውታል።

የዚህ "ጥምረት" ዓላማው ምንድነው? ስንል በሌላ አነጋገር የህወሓት አመራር ዓላማው ምንድነው? ማለትም ስለሆነ በዚህ አግባብ መጠየቁ ጉዳዩን በሰላ መልኩ ለመረዳት ያስችላል።

በማኒፌስቶው (ከገፅ 8 እስከ 11) እንደተዘረዘረው የጥምረቱ ዓላማዎች፣

ሀ/ ሰላምና የህግ የበላይነት በሀገራችን ማስፈን፣
ለ/ ህገ-መንግስቱን መጠበቅ፣ መከላከልና ህገ-መንግስታዊ ስርኣቱን ማስቀጠል
ሐ/ ህብረ-ብሄራዊ ፌደራል ስርዓቱን ማስቀጠል፣
መ/ የ2012 ዓ/ም* አገር አቀፍ ምርጫ በምንም ዓይነት ምክንያት እንዳይራዘምና እንዳይጭበረበር መታገል..... እያለ ይቀጥላል።

"በማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ!" አለ አያ ጅቦ ሆነና፤ እነዚህ ከላይ በከፊል የጠቀስናቸው እንደ ዓላማ የተቀመጡት መርሆዎችን ሲያፈርስና ሲጎድ የነበረው አካል ማን ሆኖ ነውና?! አሁን ደርሶ ጠበቃ ሊሆን የሚሞክረው።

ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-940-79-08-22/+251-914-73-35-39
Website: tigraydemocraticparty.com, email: tigraydemocraticparty@gmail.com
የካ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 13፣ ኣያት ጌት ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቤ.ቁ. 519፣ አዲስ አበባ፣
ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቤ.ቁ. 59፣ መቐለ

ሃገራችን ከባድ ቀውስ ውስጥ የከተተው የነዚህ መርሆዎች ለ27 ዓመታት በተከታታይ ማኮላሸት ያስከተለው ጦስ አይደለም እንዴ?

መራራ ሃቁ እንዲህ ነው!

1ኛ- የግለሰቦች የበላይነት በመስፈኑ-- የህግ የበላይነት ቦታ አጣ። ህግ በግለሰብ የሚቸር፣ በገንዘብ የሚተመን ሸቀጥ ሆኖ አረፈው። ይባስ ብሎም ህግ ደላላዎች እጅ ወደቀች። ነብሰ-በላ ደላላዎች የሀገሪቱን ፖለቲካና ኢኮኖሚ በቁጥጥራቸው ስር አስገብተው በቀላሉ የማይሸር ቀውስ ተፈጠረ። ይህም ለስርዓት አልበኝነት በር ከፍቶ አስነዋሪ የመንጋ ድርጊቶች እንድናይ ተገደድን።

ስለዚህ የህወሓት አመራር በየትኛው መለኪያ ነው የሰላምና የህግ የበላይነት መርህ አራማጅ ሆኖ ለመቅረብ የሚከጅለው?

2ኛ- "የአሳ ግማቱ ከአናቱ" እንዲሉ ሕገ-መንግስቱን መጠበቅና ማስከበር ተቀዳሚ ስራቸው ማድረግ የነበረባቸው የህወሓት አመራር እራሳቸው ሕገ-መንግስቱን እየጣሱ ባሻቸው ሰዓት ሕግ ተብዬ ማዘዣ እያወጡ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን፣ ጋዜጠኞችን፣ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን በአጠቃላይ ዜጎችን ሲያፍኑ፣ አስረው ሲያሰቃዩ፣ ሲገድሉ እና በሙስና ተነክረው ያለአግባብ ሲበለፅጉ የኖሩ አይደሉም እንዴ?! አሁን በምን ተአምር ወይም መለኪያ ነው ለሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ተሟጋች መስለው የሚቀርቡት። የራሳቸው ግምገማና የራሳቸው አመራር አባል የነበሩ አቶ ብርሃኑ ፅጋብ የፃፉት "የኢህአዴግ የቁልቁለት ጉዞ" በተሰኘው መፅሀፋቸው እንደሚያስረዱት በሕገ-መንግስቱ ጥሰትና በሙስና መስፋፋት ዋናው ተጠያቂዎቹ የህወሓት አመራር ለመሆኑ ፍንትው አድርገው ስላስቀመጡት ሌላ ማስረጃ ፍለጋ መሄድም የለብንምና። ሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ማስቀጠል የሚለው ዲስኩር ተራ ማጭበርበር ነው ብለን እናልፈዋለን።

3ኛ- ህብረ-ብሄራዊ ይሁን ሌላ ዓይነት ፌደራል ስርዓት የሚዋቀረው በአባላቱ ፍላጎት፣ እኩልነታዊና ቀጥተኛ ተሳትፎ ነው። ይህም ማለት ዴሞክራሲያዊ አሰራርን መሰረት በማድረግ ነው፤ ዴሞክራሲን መሰረት ያላደረገ ፌደራል ስርዓት ዘላቂ ፌደራሊዝም ሊሆን አይችልም። ስለዚህም የህወሓት አመራር በተፈጥሮውና በሂደት እንደምንገነዘበው ከዴሞክራሲያዊነት ጋር የተጣላ ስለሆነ የእውነት ፌደራል ስርዓትን ሊያስቀጥል ይቅርና ሊጀምረውም አይቻለውም። በሀገራችን የሰፈነው ስርዓት የህወሓት አመራር ከማዕከሉ በሚልካቸው ታማኝ ካድሬዎች አማካይነት የሚመራ ክልላዊ አስተዳደር እንጂ ወደ ፌደራል ስርዓት የተጠጋም ውቅር አልነበረም።

4ኛ- የ2012 ዓ/ም[ቱ] ምርጫ "እንዳይራዘምና እንዳይጭበረበር" ይሉናል! ምርጫ ማለት አንድ የዴሞክራሲ አሰራር ክፍል ነው። በተፈጥሮው ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ አካል የእውነት ምርጫ ሊያካሂድ አይችልም። ያለፉት ምርጫዎች የዚሁ ሃቅ ገላጮች ናቸው። የህወሓት አመራር ምርጫው "እንዳይጭበረበር!" ሲል ያለፉት ምርጫ ተብዬዎች እንዴት እንደተከናወኑ ህዝቡ አያውቀውምና እንደገና ላሞኛቸው ብሎ ከሆነ ክፉኛ ተሳስቷል። የራሱን ሞኝነት እያጋለጠ ነው ያለው።

ምርጫው "እንዳይራዘም!" የሚለው ጩኸትስ ለምንድነው የሚያሰማው?! የህወሓት አመራር አሁንም ምርጫውን ለማጭበርበር የሚያስችል የበላይነት ያለው ይመስለዋል፣ ህዝቡም እየነቃና እየተደራጀ በመምጣቱ፣ አማራጭ

ተወዳዳሪ ሃይሎችም ስለተፈጠሩ፣ ሆኖም ቀረ እንግዲህ እንደለመደው አሸንፌ ወጣሁ ሊያስብል የሚችልበት ወቅት ሳያመልጥ ብሎ ማስላቱ ነው።

ለዚህም ነው የትዴፓና የዓረና-ትግራይ ፓርቲዎች ከህዝባቸው ጋር በነፃነት ተገናኝተው አማራጭ ሃይሎች ሆነው እንዳይቀርቡ የህወሓት አመራር የቁም ስቃይ እያሳያቸው የሚገኘው! እውነት ያልተጭበረበረና ያልተራዘመ ምርጫ ፈላጊ ቢሆንማ ኖሮ የፖለቲካ ምህዳሩን ነፃ አድርጎ ለእውነተኛ ውድድር በቀረበ ነበር። በአማራጭ የሃሳብ ውድድር አያምንም፤ ሃሳብን ይፈራል፤ ማጭበርበሩን እንዲቀጥልበት ግን ምህዳሩን ተቆጣጥሮ ተፎካካሪዎቹን አፍኖ ይዞ ይገኛል። በዚህ ሁኔታ ምርጫ ማካሄድ ከቶውንም አይቻልም! አይቻልም! አይቻልም! እንደድሮው የምርጫ ትያትር ግን መተወን ይቻል ይሆናል። "በምንም ዓይነት ምክንያት ምርጫው አይራዘምም!" እያለ የህወሓት አመራር የሚወተውተውና የሚያቅራራው አሁን ጉልበቱ አለኝና ለማጭበርበር ይመቸኛል ከሚለው መላ-ምት ነው።

ማኒፌስቶው በመጨረሻ (በገፅ 11-12) የጥምረቱ ስትራቴጂና የትግል ስልት አስቀምጧል። ቃል በቃል ሲቀመጥ "ቀልባሽና አሐዳዊያን ሃይሎች በተፃራሪነት፣ ሕብረ-ብሄራዊ ፌደራሊስት ሃይሎች በመሪነት፣ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በዋና ሃይልነት የሚሰለፉበት ስትራተጂ ይከተላል" ይላል። ወረድ ብሎም "ሕብረ-ብሄራዊ ፌደራላዊ ስርዓት ለመቀልበስ የሚፈልጉ የመንግስትና የፓርቲ አመራሮችና አጋሮቻቸው ታግሎ፣ ቅልበሳውን ማክሸፍ....." ይልና ቀጥሎም "..... ሁሉንም ዓይነት ሰላማዊ፣ ፖለቲካዊና ህጋዊ ትግል ያካሂዳል" በማለት በማኒፌስቶው ያውጃል።

ከዚህ እወጃ እንደምንገነዘበውና ቀደም ሲል ሚያዝያ 4፣ 2011 ዓ/ም የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ መግለጫ እንዲሁም ታሕሳስ 26፣ 2012 ዓ/ም የህወሓት አስቸኳይ ጉባኤ መግለጫ እንደሚያትተው የህወሓት አመራር ባጭሩ ከለውጡ በፊት ወደነበርኩበት የስልጣን ማማ መመለስ አለብኝ እያለ ነው። ምክንያቶቹ ግን እራሱ ሲጥሳቸው የነበረው ሕገ-መንግስትና "ፌደራል ስርዓቱ ማስቀጠል ስለሚል አሁን በምን ቁመናው ነው ይኸንን ማስቀጠል የሚችለው የሚለው ጥያቄ ቢነሳ መልስ ሊያገኝ አይቻለውም። ይህ ብቻ አይደለም! "ቀልባሽና ጨፍላቂ ሃይሎች" ብሎ የፈረጃቸው ወገኖች የለውጥ ሃይሎችን የሚመለከት መሆኑ ደግሞ አያጠያይቅም።

በመግለጫዎቹ እንደምናየው እነዚህ የለውጥ ሃይሎችን በሚገርም ሁኔታ የማይመጥናቸው ስም ሰጥቷቸዋል። "አሃዳዊያን"፣ "ባንዳዎች"፣ "ከሃዲዎች"፣ "እንክርዳዶች" ቢላቸውም እነዚህ ቅፅሎች ከለውጡ ወገኖች ምንም ዓይነት ተያያዥነት ስለሌላቸው የህወሓት አመራር አንዴም የሚናገረውን የማያውቅ የዞረበት ቡድን መሆኑ፣ አልያም ጠላትን ፍለጋ የፈጠረው ጠብ አጫሪነት ዘይቤ መሆኑ ያመላክታል። ለዚህ ደንባራ አካሄድ ይረዳው ዘንድም የትግራይ ህዝብን ገፈት ቀማሽና መሳሪያው ለማድረግ "በጠላት ተከበሃል!" ታጠቅ!" "ክተት!" እያለ ሌት-ተቀን እያስጨነቀው ይገኛል። 45ኛው የትግሉ ዝክረ-በዓል አስታክከ የጦር መሳሪያ የታጠቀ ሰልፈኛ አደባባይ አስውጥቶ የጦርነት ቀረርቶና ሽለላ እያሰማ የህዝቡን ስሜት በመስለብ ላይ ይገኛል። የሚገርመው ግን ለጦርነት የተዘጋጀ ተፃራሪ ሃይል እስካሁን ድረስ የለም።

መገንጠልን (*De-facto* state) እንደ አማራጭም ለትግራይ ህዝብ አቅርቦለታል፤ የትግራይ ህዝብ ለእኩልነት፣ ለፍትህ፣ ለአንድነት ሲል ያካሄደውን ትግል የህወሓት አመራር ዋጋ አሳጥቶታል። የህዝቡም ህልም ተቀለበሰና በመዳፉ ስር ወድቆ የድህነትና የመከራ ፅዋውን እየተጋተው ይገኛል። ህዝቡ ከዚህ መከራ ለመውጣት እልህ የተሞላበት ትግል እያካሄደ ቢሆንም በመላ ኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ የነበረው የአፈና መዋቅር አሁን ጠቅልሎ ትግራይ ውስጥ በመከማቸቱ

ትግሉ ከባድ እንዲሆን አድርጎታል። የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶና ፀንቶ የሚኖር ህዝብ ነው፤ ለዚህም ነው የጋራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመመስረት የመላ ኢትዮጵያ ህዝብ ትብብርና ድጋፍ አስፈላጊ የሚሆነው!!

የህወሓት አመራር በስመ "ፌደራሊስት" ያሳባሰባቸው ቡድኖች ወደ መቐለ እያመላለሰ ቀለብ በመስፈር ወደ ነበረበት ማማ ለመመለስ ሴራ መጎንጎን ተያይዞታል። ለአገር የሚበጅ የፌደራል ስርዓት ይፈጥራሉ ማለት ዘበት ነው። "ተኩላና በግ" በአንድ በረት መክተት ማለት ስለሚሆን የህወሓት አመራር የጨለመበት ስለሆነ ሴራ ከማቀናበር ያለፈ ቁምነገር ሊኖራቸው አይችልም። ለዚህም ነው የህወሓት አመራር ውጥረት አይሎበት በ11ኛው ሰዓት የፈጠረው "ያላቻ-ጋብቻ" እንደ እምቧይ ካብ ፈራሽ የሚሆነው!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ይለምልም!!

ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ)

የካቲት 2012 ዓ/ም

ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-940-79-08-22/+251-914-73-35-39
Website: tigraydemocraticparty.com, email: tigraydemocraticparty@gmail.com
የካ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 13፣ ኣያት ጌት ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቤ.ቁ. 519፣ አዲስ አበባ፣
ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቤ.ቁ. 59፣ መቐለ